**27.07.2018**

# ቃል-ኪዳን! ከማን ጋር?

የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በተመለከተ በሓምሌ ወር የምንሰማው ዜና የሚያስደንቅ ፍጥነት ያለው ነው። ለዚሁም ግንኙቱ ምን ያህል ጥልቀትና ዕድሜ ሊኖሮው ይችላል፡ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ይመስለኛል።

ለመሆኑ አዲስ ጋብቻ ብለን እንጥራው ወይም ሁለተኛ?

በበለጸጉ አገሮች ልጅን እንኳን ለትምህርት - በትምህር-ቤት - ከማስገባታቸው በፊት ምን ያህል ጥረትና ግዜ እንደሚስፈልጋቸው እንታዘባለን። የሚገርመው ለብዙ ሺ ህዝብ የህይወት መጥፋትና ጠንቅ የሆነው ከሃያ ዓመት በፊት የተጀመረው የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት አሁን የምንሰማውን ያህል ፍጥነት የነበረው መሆኑን አስታውሳለሁ።

የማያከራክር እውነት፡ የሁለቱ አገሮች ህዝቦች በባህልም በትውልድም ያላቸው መቀራረብ ነው። አሁን ለሚታቀድ ግንኙነት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ወሳኝ ሊሆኑ ግን አይችሉም። ወሳኙ የህዝቦች አመለካከትና ፍላጎት መሰረት ያደረገ፣ በህግ ባለሞያዎች የተጠና፣ በሕዝብ ተወካዮች የጸደቅና የሚከበር፣ ውል ሲኖር ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፤ በበለጸጉ አገሮች ወላጆችና ልጆች የጋራ-ንበረት ወይም የጋራ ድርጅት ሲነራቸው፣ ፍርድ-ቤት የሚያውቀው ውል ይኖራቸዋል። ውል አለማክበር የሚያስከትለው ኪሳራም ግልጽ ይደረግላቸዋል።

በ**1961** ዓ.ም.ፈ የተጀመረው የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት ጠንቅም፡ አጼ-ሃይለስላሴ የፈደረሽን ውል እንዲፈርስ ማድረጋቸው መሆኑን በቅርብ የተከታተሉት ፕሮፌሶር በረከት ሃብተስላሴና ሻለቃ ዳዊት ወልደገርጊስ ይገልጹታል። ለዚሁም የጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር አቢይና የፕረሲዳንት ኢሰያስ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጉብኝቶችና ንግግሮች በጥልቅ መገምገም አስፈላጊ ነው።

የክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ የአስመራን ጉብኝት ከልብ ነው የምደግፈው። ዕጣችን የስሃራ በረሃና የሜዲተራንያን ባህር ነው ለሚሉ ልጆቻችንም የተስፋ ጩራን ነው። ለክቡር ጠቅላይ ሚንስትር በከተማው የተደረገው ደማቅ አቀባበል ሰምተናል። በክፍለ ዓለማችን ደማቅ አቀባበል መገምገም ቀላል አይደለም። በቀበሌ ተገደህም እንግዳ መቀበል የተለመደ ሰለሆነም ነውና።

የክቡር ኣቶ ኢሰያስ የኢትዮጵያ ጉብኝት በተመለከተ የኣዋሳ ከተማ ንግግራቸውም ክብርና ፕረቶኮል ያልጠበቀ መኖሩን ለመገንዘብ ችያለሁ። ለክቡር ዶክተር ኣቢይ፦ "ከዛሬ ጀምሮ የምትመራን ኣንተ ነህ"፣ ስልጣን ኣስረክቤህ ኣለሁ"፣ የሚል ኣነጋገር፡ ስልጣኑ ራሳቸው የነጠቁት እንጂ የኤርትራ ህዝብ እንዳልሰጣቸው ያመለክታል። የቈሳቊስ ስጦታ እንጂ የፕረሲደንትነት ስጦታ ማስረከብ ከሳቸው ብቻ ነው የሚሰማ።

ክቡር ኣቶ ኢሰያስ በኣመሪካ ኣገር የስራ ጉብኝት ባደረጉት ወቅትም ከኣመሪካ ድምጽ-ረድዮ (VOA) ለቃለ-መጠይቅ ቀርበው ጋዜጠኛው፡ በኤርትራ የፕረሲዳንት ምርጫ መቼ ይደረጋል፣ ብሎ ሲጠይቃቸው፦ "ለኔ ስልጣኑ በኮንትራት የሰጠኝ የለም" የሚል ቃል መስጠታቸው ይታወሳል። የሓምሌ ወር የኣዲስ ኣበባ ንግግራቸውም፣ "እርጋታችን በመሸበርና ልማትና እድገታችን ለመውደም፡ ለማንም ቢሆን ኣንፈቅድም" የሚል ነበር። ኣሁንም ቢሆን ለሁለቱም ኣገሮች ህዝቦች ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ፡ ለሰላም፣ ለድርድርና ለጋራ ጥቅም መጠበቅና ማስከበር የሚል ኣስተሳሰብ፡ ከሳቸው የራቀ ይመስላል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ከሁሉም የኣገሪቱ ተወካዮች፡ ከኢንቨስትሜንቱ እቅድ ባሻገር በእኩልነትና በመከባበር መልካም ጉርብትና እንዲኖር፡ ረጋ ብሎ የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት መፈተሽ፡ በጣም ኣስፈላጊ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በኔ ኣመለካከት፡ ከቡር ኣቶ ኢሰያስ ችላ ቢሉትም፡ የኣገሮቹ ድንበር ጥያቄ መመለስ ለጓደኝነትና ኣብሮ ለመስራት ይበጃል ባይ ነኝ። የቀድሞ የግድ ጋብቻ፡ ውጤቱ ድህነትና ሞት መሆኑን ኣይተነዋል። የዓይን ምስክሮችም ነን። የኤርትራ ህዝብም ኣሁን ድርሻው ካላበረከተ፣ የጋዜጠኛው በዓሉ ግርማ መጽሓፍ "ኦሮማይ" ማንበብ ኣይጠቅመውም። ኣዲስ ቢጻፍም ኣንባቢ ኣያገኝም።

ሞገስ ሃብተማርያም
ጀርመን